# ከድጡ ወደማጡ

የዘንድሮስ ምርጫ ፤ ጭራሽ . . አይን አወጣ
መሳለቂያ ሆነ ፤ እንዲያው የለበጣ
ሀጎስ ተሰናብቶ ፤ ሀጎስ ስለመጣ
ዛሬም ወያኔ እንጂ ፤ መቼ ለውጥ ሊመጣ
በህዝብ መቀለድ ፤ ሰው ስራ ፤ መች አጣ
ለምን አይወስዱትም ፤ እንደ እቁብ . . በእጣ ።

የጎጠኞች ጎጆን ፤ ቀለም በመቀባት
ህወሀት ተባሮ ፤ አረናን ማስገባት
መለሰን ሸኝቶ ፤ ስዬን በመተካት
ስህተትን መድገም ፤ ሁለተኛ ጥፋት
ዛሬም አለመማር ፤ ላያተርፉ ልፋት
የቀድሞ ወያኔን ፤ ሥም ቀይሮ . . ማምጣት
ያሁኑማ ባሰ ፤ ወይ . . ህሊና ማጣት
እራስን አዋርዶ ፤ እራስን ማሳጣት ።

ሁሉም . . ነፍሰ በላ ፤ ከጫካ የወጡ
አልተገራ አፋቸው ፤ ያልተቆነጠጡ
ጦርነት ፈጣሪ ፤ በህዝብ ያላገጡ
የኢትዮጵያን ልጆች ፤ በልተው ያላመጡ
አገርን ለማፍረስ ፤ ምለው የቆረጡ
ባህር በር ፤ ያሳጡን ፤ ዳር ድንበር . . የሸጡ
ስዬም ሆነ . . ገብሩ ፤ መቼ ተለወጡ
ዞሮ . . ወያኔ ነው ፤ ምን ቢገላበጡ
እነሱን ለመሾም ፤ መድከሙ መሮጡ
ተሽቆልቁሎ መውረድ ፤ ከድጡ ወደማጡ ።

ታዛቢው … March, 18, 2010